የሰ/መ/ቁ. 51295

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዮሐንስ ጡእማይ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ምህረት ገብሩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ባልና ሚስት በትዳር ወቅት እያሉ አንደኛው ተጋቢ ከሌላው ተጋቢ እውቅና ውጪ ብድር ተበድሮ ሲገኝ ብድር የጋራ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በውቅሮ በደደቢት ጣቢያ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የአመልካች የካቲት 01 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ የጋራ ንብረት ክፍፍልም በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፈፀምልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ጋብቻው በፍቺ በፍርድ ቤት ቢፈርስ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን፣በጋራ ንብረት ክፍፍልም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ በፈፀሙት የጋብቻ ውል መሰረት እኩል በእኩል እንዲካፈሉ፣በጋብቻ ወቅት የተወለዱት ሦስት ልጆች ከተጠሪ ጋር እንዲያድጉ ሆኖ ቀለብን በተመለከተ ግን ለእያንደንዳቸው በወር ብር 70.00(ሰባ ብር) አመልካች እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ አመልካች ለአሁኑ ክርክር መሰረት የሆነው ማረት ከተባለ ድርጅትና ከዳሽን ባንክ የተወሰነውን የብድር እዳ በተመለከተ ተጠሪና አመልካች በጋራ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን በጋራ እንዲከፍሉት፣እዳው ከተቀነሰ በኋላ የንብረት ክፍፍልም እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለውቅሮ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ሰበር ሰሚው ችሎት የንብረት ክፍፍልን በሚመለከት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሲያፀና በስር ፍርድ ቤቶች የጋራ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ግን አመልካች የተበደሩትን ብር በሚመለከት ተጠሪን ሳያሳየው የተበደሩት፣የተበደሩትም ብር በጋራ ጥቅም መዋሉን ያላስረዱ እና እንዲሁም የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ቤት የሆነውን አመልካች ከዳሽን ባንክ ለተበደሩት ብድር አከፍፈል ለዋስትና ሲያስይዙ የተጠሪን ፈቃድ አልጠየቀም የሚሉትን ምክንያቶች በመያዝ አመልካች ከዳሽን ባንክ የተበደሩትን ብር 65,000.00(ስልሳ ስምንት ሽህ ብር) የአመልካች የግል እዳ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ብድሩ መኖሩን አውቀው ከስምንት ወራት ያህል እዳውን ከአመልካች ጋር ሲመልሱ የነበሩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ እና አመልካች ነጋዴ በመሆናቸው የተጠሪን ፈቃድ ሳይጠይቁ ብድር መበደርና የጋራ ንብረትን በዋስትና ማስያዝ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ የተጠሪ ፈቃድ ያልተጠየቀበት እና እዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ እዳው ተጠሪን አይመለከታቸውም መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአንድ በኩል የአመልካች በንግድ ስራ ከመሰማራታቸውና በሌላ በኩል ደግሞ የባንክ ብድሩ የተወሰደው ግራ ቀኝ በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ብድሩ ለጋራ ጥቅም አልዋለም ተብሎ ተጠሪ ከእዳው ነፃ እንዲሆኑ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጕአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ፀንተው በነበሩበት ወቅት አመልካች በንግድ ስራ ተሰማርተው የነበሩ መሆኑን፣በዚህም ወቅት አከራካሪውን ብድር ተጠሪን ሳያሳውቁ የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረት በዋስትና አስይዘው መውሰዳቸውን፣ከትዳር ላይ እያሉም የተወሰነውን የብድሩን ገንዘብ መመለሳቸውን ነው፡፡

አመልካች በንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴ ከሆኑ ብድሩን በሚበደሩበት ወቅት የተጠሪን ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው ሊባሉ የማይችሉ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 16 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪ እዳው መኖሩን ያውቁ የነበረ ስለመሆኑም በወቅቱ የብድሩን ገንዘብ በጋራ መመለሳቸው የሚያረጋግጠው ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ብድሩ አመልካች ነጋዴ ሆነው በትዳር ወቅት ወስደው በጋራ ሲከፈል የነበረ በመሆኑ የተጠሪ ፈቃድ የለበትም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በእርግጥ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት የሆነ አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት ሐብትነትን ወይም ሌላ መብት ለ3ኛ ሰው ለማስተላለፍ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት ማስፈለጉ በቤተሰብ ሕጉ የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ የሚችል መሆኑን የቤተሰብ ሕጉ ደንግጕ እናገኘዋለን፡፡ የሕጉ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የማይወስድ ነው፡፡ ይልቁንም ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ እስካላደረገው ድረስ ውሉ ውጤት ይኖርዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች ነጋዴ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ብድሩን ተጠሪ እያወቁ ለተወሰነ ጊዜ አብሮ ሲከፍሉ የነበረ፣ውሉን እንዲፈርስ ያላደረጉት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕግ ግምት የሚወስድበት ሲሆን ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪ እንጂ አመልካች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቱ የብድር እዳው የጋራ ነው ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ባግባቡ ከንግድ ሕጉ እና ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስ ሳያገናዝብ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30245 ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከዳሽን ባንክ እና ከማረት ማህበር የወሰዱት ብድር የጋራ እዳ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡